የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሰባተኛ ዓመት q_R &9
አዲስ አበባ ሰኔ 07 qN 2ሺ3 ዓ.ም

bx}T×eÃ ØÁ‰§ê Ä}äK‰s}Ãê ¶pBI}K
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የwÈ

17th Year No. 79
ADDIS ABABA 24th June, 2011

¥WÅ

xê J q_R 7)05/2ሺ3

የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ .....ገጽ 5¹}9)%9

CONTENTS

Proclamation No. 715/2011

Private Organization Employees Pension Proclamation …Page 5969

አዋጅ ቁጥር 7)05/2ሺ3

ስለግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

የማህበራዊ ዋስትናን ስርዓት በማስፋፋት ደረጃ በደረጃ ለዜጎች እንዲዳረስ ማድረግ ከአገሪቷ ማህበራዊ ፖሊሲ አንዱ አካል በመሆኑ፤

የስርዓቱ መስፋፋትና ተጠናክሮ መቀጠል ለማህበራዊ ፍትሕ፣ ለኢንዱስትሪ ሰላም፣ ለድህነት ቅነሳና ለልማት ጉልህ አስተዋፆ ስለሚኖረው፤

የግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ $5(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 7)05/2ሺ3" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

PROCLAMATION No. 715/2011

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR PENSION OF PRIVATE ORGANIZATION EMPLOYEES

WHEREAS it is part of the country's social policy to expand the social security system and reach citizens step by step;

WHEREAS the strengthening and sustainability of the system greatly contributes to social justice, industrial peace, poverty reduction and development;

WHEREAS it has been found necessary to put in place private organization employees pension scheme;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Private Organization Employees Pension Proclamation No. 715/2011".

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ "የግል ድርጅት ሠራተኛ" ማለት ማንኛውም በግል ድርጅት በቋሚነት በመቀጠር ደመወዝ እየተከፈለው የሚሠራ ሰው ነው፤

2/ "ቋሚ ሰራተኛ" ማለት በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 3)&7/09)(6 ላልተ ወሰነ ጊዜ ለተቀጠረ ሠራተኛ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፤

3/ "የግል ድርጅት" ማለት ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለእርሻ፣ ለኮንስትራክሽን፣ ለማህበራዊ አገል ግሎት ወይም ለሌላ ሕጋዊ ዓላማ የተቋቋመ ሠራተኛ ቀጥሮ ደመወዝ እየከፈለ የሚያሠራ የግል ተቋም ወይም ሰው ሲሆን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ይጨምራል፤

4/ "መንግሥት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴራል መንግሥትን እና የክልል መንግሥታትን ያጠቃልላል፤

5/ "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ #7(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

6/ "የግል ድርጅት አገልግሎት" ማለት በግል ድርጅት ሠራተኞች የሚፈጸም አገልግሎት ነው፤

7/ "አበል" ማለት የአገልግሎት ጡረታ አበል፣ የጤና ጉድለት ጡረታ አበል፣ የጉዳት ጡረታ አበል ወይም የተተኪዎች ጡረታ አበል ሲሆን የዳረጎት አበልና የጡረታ መዋጮ ተመላሽን ይጨምራል፤

8/ "ደመወዝ" ማለት ለሥራ ግብርና ለማንኛውም ሌላ ጉዳይ ተቀናሽ የሚሆነው ሂሣብ ሳይነሣለት አንድ የግል ድርጅት ሠራተኛ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ለሚሰጠው አገል ግሎት የሚከፈለው ሙሉ የወር ደመወዝ ነው፤

9/ "ባለመብት" ማለት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት አበል የሚያገኝ ወይም አበል ለማግ ኘት የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች የሚያሟላ የግል ድርጅት ሠራተኛ ወይም ተተኪ ነው፤

2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "private organization employee" means a salaried person permanently employed in any private organization;

2/ "permanent employee" means an employee hired for an indefinite period in accordance with the definition assigned to it under the Labour Proclamation No. 377/2003;

3/ "private organization" means an organization established to engage in commerce, industry , agriculture, construction, social service or in any other lawful activity and which has salaried employees and includes charities and associations;

4/ "government" means the federal government and includes the regional states of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

5/ "region" means any state referred to in Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

6/ "private service" means service rendered by employees of private organizations;

7/ "benefit" means retirement pension, invalidity pension, incapacity pension or survivors' pension and includes gratuity and the refundable pension contribution;

8/ "salary" means monthly salary received by the employees of private organization, for services rendered during regular working hours without the deduction of any amounts in respect of income tax or any other matter;

9/ "beneficiary" means an employee of private organization or his survivor who receives benefits or fulfils the conditions for receiving benefits in accordance with this Proclamation;

0/ "ተተኪ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ "9 ንዑስ አንቀፅ (3) የተዘረዘሩትን ያጠቃልላል፤

01/ ‹‹የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ›› ማለት በዚህ አዋጅ ለሚሸፈኑ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ አበል ክፍያና አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ ስርዓት ነው፤

02/ "የጡረታ ፈንድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚሰበሰብ የጡረታ መዋጮና ለሚፈጸም የአበል ክፍያ ተግባር የተቋቋመ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ ፈንድ ነው፤

03/ "ኤጀንሲ" ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 2)2/2ሺ3 የተቋቋመው የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ነው፤

04/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

05/ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል::

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1/ የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን የጡረታ ጥቅም የሚመለከተው የአዋጅ ቁጥር 2)&/09)(4 ድንጋጌ እና አገሪቷ ተዋዋይ ወገን የሆነችባቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆኖ ይህ አዋጅ በዜግነት ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፡-

ሀ) ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በተቋቋሙ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ ወይም ፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ያላቸው ሠራተኞች በነ በራቸው ዐቅድ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚነታቸውን ለመቀጠል ሊወስኑ ወይም በዚህ አዋጅ ስለሚሸፈኑበት ሁኔታ ሊስማሙ ይችላሉ፤

10/ "survivor" includes persons mentioned under Article 39(3) of this Proclamation;

11/ "private organization employees pension scheme" means a system established to pay benefit and provide service to employees covered by this Proclamation;

12/ "pension fund" means fund established for the purpose of collecting pension contributions and effecting benefit payments pursuant to this Proclamation;

13/ "Agency" means the Private Organization Employees Social Security Agency established by the Council of Ministers Regulation No. 202/2011;

14/ "person" means any natural or juridical person;

15/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

3. <u>Scope of Application</u>

1/ Without prejudice to the appropriate provisions of the Proclamation No. 270/2002 that provide pension coverage to foreign nationals of Ethiopian origin and international agreements to which the country is a party, this Proclamation shall be applicable to employees of private organizations who are Ethiopian nationals.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article:

a) employees, who have pension scheme or provident fund before the coming into force of this Proclamation, may either decide to continue to benefit from the pension scheme or the provident fund or agree to be covered by this Proclamation;

ለ) የሃይማኖት ድርጅቶች እና የፖለቲካ ድርጅቶች ሠራተኞች እና መደበኛ ባልሆነው የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ሰዎች በፈቃደኝነት ላይ ተመሥርቶ በዚህ አዋጅ መሠረት የጡረታ ሽፋን እንዲያገኙ ይደረጋል።

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም፡-

ሀ) የቤት ሠራተኞች፤ እና

ለ) መንግሥታዊ የዓለም አቀፍ ድርጅቶችና የውጭ መንግሥታት ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ሠራተኞች፤

በዚህ አዋጅ አይሸፈኑም።

ክፍል ሁለት
ስለማህበራዊ ዋስትና ምዝገባና መለያ ቁጥር

4. ምዝገባ

1/ ማንኛውም የግል ድርጅት የተቋቋመበትን ህግ፣ የግል ድርጅቱ ሠራተኛ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር የሞላውን የሕይወት ታሪክ፣ የተሰጠውን የቅጥር ደብዳቤ እና ሌሎች በኤጀንሲው የሚወሰኑ መረጃዎችን ለምዝገባ ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚቀርቡ የምዝገባ ማስረጃዎች፡-

ሀ) ነባር የግል ድርጅቶችንና የግል ድርጅት ሠራተኞችን የሚመለከቱ ሲሆን ኤጀንሲው በሚወስነው የጊዜ ገደብ ውስጥ፤

ለ) ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን በኋላ የተቋቋመ የግል ድርጅት ወይም የተቀጠረ የግል ድርጅት ሠራተኛን የሚመለከት ሲሆን የግል ድርጅቱ በተቋቋመ ወይም ሠራተኛው በተቀጠረ በ% ቀናት ውስጥ፤

መቅረብ አለባቸው።

5. የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር

1/ ማንኛውም የግል ድርጅት ወይም የግል ድርጅት ሠራተኛ የምዝገባ ማስረጃ ተሟልቶ ሲቀርብ የማህበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ይሰጠዋል፤ ሆኖም የግል ድርጅቱ ወይም ሠራተኛው የታክስ መለያ ቁጥር ካለው ይኸው ቁጥር የማኅበራዊ ዋስትና መለያ ቁጥር ጭምር ሆኖ እንዲያገለግል ይደረጋል።

b) employees of religious organizations and political organizations and persons engaged in the informal sector shall, upon their consent, be covered by this Proclamation.

3/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, this Proclamation shall not be applicable to:

a) domestic workers; and

b) employees of governmental international organizations and foreign diplomatic missions.

PART TWO
SOCIAL SECURITY REGISTRATION AND IDENTIFICATION NUMBER

4. Registration

1/ Any private organization shall, for the purpose of registration, submit to the Agency copies of its establishment law, personal data of its employee taken at the time of first employment, letter of employment issued to the employee and other particulars determined by the Agency.

2/ The time limit for submission of data in accordance with sub-article (1) of this Article shall:

a) in the case of existing private organizations and their employees, within the time to be determined by the Agency;

b) in the case of private organizations established, or employees of private organizations employed after the effective date of this Proclamation, within 60 days from the date of establishment or employment.

5. Social Security Registration Identification Number

1/ Any private organization or an employee shall, upon submission of complete data for registration, be assigned with social security identification number; provided, however, that the tax identification number of the private organization or employee, if any, shall also be taken as social security identification number.

2/ ማንኛውም የግል ድርጅት ሠራተኛ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን ባለው የግል ድርጅት ሲቀጠር የማህበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥሩን ለተቀጠረበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የግል ድርጅት የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

6. የምዝገባ መረጃ ለውጥን ስለማሳወቅ

1/ ማንኛውም የግል ድርጅት የራሱንና የግል ድርጅት ሠራተኛውን የምዝገባ መረጃ የሚመለከት ለውጥ ሲያጋጥም ለውጡ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ% ቀናት ውስጥ የተከሰተውን ለውጥ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር አያይዞ ለኤጀንሲው በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ እያንዳንዱ የግል ድርጅት ሠራተኛ የቤተሰብ ሁኔታን የሚመለከት የመረጃ ለውጥ ሲያጋጥመው ከደጋፊ ማስረጃ ጋር ለሚሰራበት የግል ድርጅት በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

3/ አበል በመቀበል ላይ የሚገኝ ባለመብት በምዝገባ መረጃው ላይ ለውጥ ሲያጋጥመው ለውጡ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በ% ቀናት ውስጥ ከደጋፊ ማስረጃ ጋር ለኤጀንሲው በማቅረብ ማሳወቅ አለበት፡፡

4/ ማንኛውንም የግል ድርጅት፣ የግል ድርጅት ሠራተኛ ወይም ባለመብት የሚመለከት የምዝገባ መረጃ ለውጥ ማሳወቂያ ሲቀርብ የማህበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥሩ መጠቀስ አለበት፡፡

5/ የማህበራዊ ዋስትና የምዝገባ መለያ ቁጥር የተሰጠው የግል ድርጅት ሲፈርስ፣ ሲከፋፈል ወይም ከሌላ ጋር ሲቀላቀል፡-

ሀ) ስለመፍረሱ፣ የፈረሰዉ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ የነበረዉ ወይም አጣሪዉ፤

ለ) ስለመከፋፈሉ ወይም ስለመቀላቀሉ፣ ሠራተኞቹን የተረከበዉ የግል ድርጅት፤

ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት % ቀናት ውስጥ ይህንኑ ለኤጀንሲው በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ Any employee of private organization, when employed by a public office or another private organization covered by social security scheme, shall notify his identification number to such office or organization.

6. Notification of Changes in Entries of Registration

1/ Any private organization shall, when change of entry of its organization or employee occurs, notify such change to the Agency, with supporting evidence, within 60 days of the occurrence of such change.

2/ Every employee of private organization shall notify, with supporting evidence, to the private organization that he is working for, any change regarding his family status.

3/ Any beneficiary who is receiving benefit shall notify, with supporting evidence, to the Agency any change in the entries of social security registration within 60 days of the occurrence of such change.

4/ Any notification of change in the entry of social security registration relating to a private organization, employee or beneficiary, shall indicate the corresponding social security identification number.

5/ Where a private organization to which a social security registration identification number is assigned has been dissolved, divided or amalgamated, the following shall notify same to the Agency, with supporting document, within 60 days from the date of the decision to such effect:

a) the former Director or the liquidator, in the case of dissolution;

b) the private organization to which employees have been transferred, in the case of division or amalgamation.

7. ማስረጃን አለማቅረብ የሚያስከትለው ውጤት

1/ በዚህ ክፍል በተመለከተው መሠረት የሠራተኛ ማስረጃ አደራጅቶ የማይዝና በወቅቱ ለኤጀንሲው የማያስተላልፍ የግል ድርጅት የሚመለከተዉ ኃላፊ በዚህ አዋጅ አንቀጽ $9 መሠረት ይቀጣል፡፡

2/ በዚህ ክፍል በተመለከተው መሠረት የለውጥ ማስረጃን በወቅቱ ለማያቀርብ የግል ድርጅት ሠራተኛ ወይም ባለመብት ለተተኪዎቹ የሚወሰነው አበል አስቀድሞ በኤጀንሲው ተደራጅቶ በተያዘው መረጃ መሠረት ይሆናል፡፡

ክፍል ሦስት
ስለጡረታ ዐቅድ፣ ፈንዶችና መዋጮዎች

8. የግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ መቋቋም

የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

9. ስለጡረታ ፈንድ መቋቋም

1/ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3/2//ሀ/ መሠረት ስምምነታቸውን የገለጹ የግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ወደ ተቋቋመው የግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ይዛወራል፡፡ ሆኖም በዚህ አዋጅ መሠረት መከፈል ከሚገባው መጠን በላይ የተከፈለ የጡረታ መዋጮ ወይም ፕሮቪደንት ፈንድ መዋጮ ቢኖር ታስቦ ለሠራተኞቹ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

0. የግል ድርጅቶች ሠራተኞች አገልግሎት ጡረታ ፈንድ መዋጮዎች

ለግል ድርጅቶች ሠራተኞች አገልግሎት ጡረታ ፈንድ በሠራተኛው ደመወዝ ላይ ተመስርቶ የሚደረገው መዋጮ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

1/ በግል ድርጅቱ 01በመቶ፤

2/ በግል ድርጅት ሠራተኛው 7በመቶ፡፡

7. Consequences of Failure to Submit Data for Registration

1/ The concerned officer of a private organization who fails to organize, keep and timely submit data to the Agency for registration as provided under this Part shall be punishable in accordance with Article 59 of this Proclamation.

2/ Where an employee of private organization or beneficiary fails to submit timely data relating to changes in entries of registration as provided under this Part, his survivors' entitlements to benefits shall be based on the data that have already been organized and kept by the Agency.

PART THREE
PENSION SCHEME, FUND AND CONTRIBUTIONS

8. Establishment of Private Organization Employees Pension Scheme

Private Organizations Employees Pension Scheme is hereby established.

9. Establishment of Pension Fund

1/ Private Organizations Employees Pension Fund is hereby established.

2/ Where employees of private organizations consented in accordance with Article 3(2)(a) of this Proclamation, their pension or provident fund shall be transferred to the Private Organizations Employees Pension Fund established under sub-article (1) of this Article; provided, however, that the contribution which is in excess of what would have been contributed in accordance with this Proclamation shall be refunded to the employees.

10. Contribution to the Private Organizations Pension Fund

The contributions payable to the Private Organizations Pension Fund shall, based on the salary of the employee of the private organization, be:

1/ by the employer, 11%;

2/ by the employee, 7%.

01. የጡረታ መዋጮ ክፍያ

1/ እያንዳንዱ የግል ድርጅት የሠራተኞቹን የጡረታ መዋጮ ከደመወዛቸው ቀንሶና የራሱን መዋጮ ጨምሮ ለጡረታ ፈንዱ በየወሩ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተገለጸው የጡረታ መዋጮ ለሠራተኞች የወር ደመወዝ ከተከፈለበት ወር መጨረሻ ቀን አንስቶ በ" ቀናት ውስጥ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ መደረግ አለበት፡፡

3/ ከሠራተኞቹ ደመወዝ ሊቀነስ የሚገባውን መዋጮ ሳይቀንስ የቀረ የግል ድርጅት ክፍያውን ራሱ ለመፈጸም ኃላፊ ይሆናል፡፡

4/ ከግል ድርጅቶችና ከግል ድርጅት ሠራተኞች የሚሰበሰበዉ የጡረታ መዋጮ ኤጀንሲው በሚወክላቸው አካላት አማካኝነት ተሰብስቦ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተሰብስቦ በቀጣዩ ወር የመጀመሪያዎቹ የስራ ቀናት ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ይደረጋል፡፡

5/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰበሰበው የጡረታ መዋጮ በትክክል ገቢ ስለ መደረጉ የመቆጣጠር ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

6/ ኤጀንሲው ወይም ውክልና የተሰጠው አካል ተገቢውን የጡረታ መዋጮ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ ሳያደርግ ከ3 ወር በላይ የቆየ የግል ድርጅትን በባንክ ካለው ሂሣብ ላይ ተቀንሶ ገቢ እንዲሆን የማስደረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

7/ ማንኛውም ባንክ በኤጀንሲው ወይም ውክልና በተሰጠው አካል ሲጠየቅ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የሚሰበሰበዉን የጡረታ መዋጮ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከግል ድርጅቱ ሂሣብ ላይ ቀንሶ ለኤጀንሲው ወይም ውክልና ለተሰጠው አካል ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

8/ በግል ድርጅቶች ጡረታ ዐቅድ ለተሸፈኑ ሠራተኞች ደመወዝ የሚከፍል አሠሪ ገንዘቡ የሚገኝበትን የባንክ ቅርንጫፍና የሂሣብ ቁጥሩን ለኤጀንሲው በጽሁፍ የማሳወቅ፣ የባንኩ አድራሻና የሂሣብ ቁጥሩ ሲለወጥም ለውጡ ከተከሰተበት ቀን አንስቶ በ05 ቀናት ውስጥ ለኤጀንሲው በጽሁፍ የመግለጽ ግዴታ አለበት፡፡

11. Payment of Pension Contributions

1/ Every private organization shall deduct contributions of its employees from their salaries and pay the amount, together with its own contributions to the Pension Fund monthly.

2/ The contributions referred to in sub-article (1) of this Article shall be paid to the Pension Fund within 30 days from the last day of the month in which payment of salary has been effected.

3/ Where the private organization fails to deduct contributions of its employees from their salaries, it shall be liable for payment of same.

4/ Contributions of private organizations and employees of private organization shall be collected within the time specified under sub article (2) of this Article by the bodies to be delegated by the Agency and paid to the Pension Fund within the first working days of the following month.

5/ The Agency shall have the power to supervise the proper computation of contributions to be collected in accordance with this Article.

6/ Where a private organization fails to pay contributions for a period of more than three months, the Agency or the delegated body has the power to cause the deduction of the arrear contributions and additional payments from the money deposited in its bank account.

7/ Any bank shall, when requested by the Agency or the delegated body, have the obligation to deduct, without any precondition, the amount of contributions to be collected pursuant to sub article (1) of this Article from the account of the private organization and pay to the Agency or the delegated body.

8/ A private organization which pays salary to employees covered by pension scheme shall have the obligation to notify, in writing, to the Agency the branch of the bank and the account number in which it has deposited money, and any change of address of the bank and bank account within 15 days of the occurrence of such change.

9/ ኤጀንሲው ወይም ውክልና የተሰጠው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (7) መሠረት ሊሰበሰብ ያልቻለን ውዝፍ የጡረታ መዋጮ ግብር የመክፈል ግዴታቸውን ያልተወጡ ግብር ከፋዮች ሃብት በመያዝና በመሸጥ የግብር አሰባሰብ የሚከናወንበትን ስርዓት ለመወሰን የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ያወጣውን መመሪያ በመከተልና በቀጥታ የግል ድርጅቱን ንብረት በጨረታ በመሸጥ ገቢ የማስደረግ ሥልጣን ይኖረዋል።

9/ In line with the directive issued by the Ministry of Finance and Economic Development to determine the rules for enabling the collection of tax by seizing and selling the property of tax payers who failed to perform their obligation to pay tax, the Agency or the delegated body shall have the power to sell, through tender, the property of the private organization for the purpose of collecting arrear contributions that could not be collected pursuant to sub-article (7) of this Article.

0/ ከጡረታ መዋጮ ገንዘብ ላይ ቀንሶ ለአገልግሎት ክፍያ፣ ለገንዘብ ማስተላለፊያ፣ ለዕዳ ወይም ለማንኛውም አገልግሎት መጠቀም የተከለከለ ነው።

10/ It is prohibited to deduct from pension contributions for payment of service charges, money transfer charges or debt or for any other purpose.

01/ ኤጀንሲው የጡረታ መዋጮ ገቢን ከመሰብሰብና ከማስፈፀም ጋር የተያያዙ ማናቸውንም ስራዎች ለሌሎች አካላት ውክልና በመስጠት ማሰራት ይችላል።

11/ The Agency may delegate any of the activities in relation to the collection and enforcement of pension contributions to other bodies.

02/ የጡረታ መዋጮ ክፍያ ከማንኛውም ዕዳ ክፍያ ቅድሚያ ይኖረዋል።

12/ The payment of contributions shall have priority over any debt.

02. <u>የጡረታ ፈንድ አስተዳደር</u>

12. <u>Administration of Pension Fund</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 የተቋቋመውን የጡረታ ፈንድ የሚያስተዳድረው ኤጀንሲው ይሆናል።

The Pension Fund established under Article 9 of this Proclamation shall be administered by the Agency.

03. <u>የጡረታ ፈንድ አጠቃቀም</u>

13. <u>Utilization of Pension Fund</u>

1/ የጡረታ ፈንዱ ጥቅም ላይ የሚውለው፡-

1/ The Pension Fund shall be utilized only for:

ሀ) በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን የጡረታ አበል ክፍያዎች ለመፈጸም፤

a) effecting benefit payments stipulated in this Proclamation;

ለ) ለትሬዠሪ ቦንድ መግዣና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ ለሚወሰኑ ሌሎች አትራፊና አስተማማኝ ኢንቨስትመንቶች፤ እና

b) investment in treasury bonds and other profitable and reliable investments to be specified by directive of the Ministry of Finance and Economic Development; and

ሐ) ለኤጀንሲው አስተዳደራዊ ወጪዎች፤ ብቻ ይሆናል።

c) covering the operational expenses of the Agency.

2/ የጡረታ ፈንዱ በማናቸውም የዕዳ ክፍያ ምክንያት ሊከበር ወይም ሊያዝ አይችልም።

2/ The Pension Fund may not be attached or secured in respect of any debt.

04. <u>የአክቸዋሪ ግምገማ</u>

14. <u>Actuarial Analysis and Evaluation</u>

የጡረታ ዕቅዱ በየአምስት ዓመቱ በሂሣብ ስሌት ባለሙያዎች እንዲገመገም ይደረጋል።

The Pension Scheme shall be evaluated by actuaries every five years.

ክፍል አራት
ስለአገልግሎት ዘመንና የጡረታ መውጫ ዕድሜ

05. የአገልግሎት ዘመን መቆጠር ስለሚጀምርበት ጊዜ

1/ የግል ድርጅት ሠራተኛ የአገልግሎት ዘመን መቆጠር የሚጀምረው በሠራተኛነት ከተቀጠረበት ቀን አንስቶ ነው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የግል ድርጅት ሠራተኛው የጡረታ ዐቅድ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ የነበረዉ ከሆነ የጡረታ ዐቅድ ፈንዱ ወይም የፕሮቪደንት ፈንዱ ለግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ገቢ ሲሆን በዚህ አዋጅ አንቀፅ 0 መሠረት ሊሸፍን በሚችለዉ የጡረታ መዋጮ መጠን አገልግሎት ይያዝለታል።

3/ የግል ድርጅት ሠራተኛው ለመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ የከፈለው መዋጮ ለግል ድርጅት ሠራተኞች ጡረታ ዐቅድ በማዛወር በመንግሥት መሥሪያ ቤት የፈጸመው አገል ግሎት እንዲያዝለት ይደረጋል። ለዚህ አገልግሎት አያያዝ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድን የሚያስተዳድረው አካል የሠራተኛውን የግል መረጃና ለመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ የተከፈለውን የጡረታ መዋጮ ገንዘብ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለግል ድርጅቶች ሠራተኞች ጡረታ ፈንድ ማዛወር ይኖርበታል።

06. የአገልግሎት ዘመን አቆጣጠር

1/ የአገልግሎት ዘመን የሚቆጠረው በሙሉ ዓመታት፣ በወራትና በቀናት ታስቦ ነው።

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 05/2/ እና /3/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለግል ድርጅት ሠራተኛ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና የግል ድርጅቶች ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ ሽፋን ባላቸው የግል ድርጅቶች የተፈጸመ የአገልግሎት ዘመን በሙሉ ተዳምሮ ይታሰባል።

3/ ለማንኛውም የግል ድርጅት ሠራተኛ የሚከተለው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፦

ሀ) ከጡረታ መውጫ ዕድሜ በኋላ አገልግሎቱ በሕግ መሠረት ተራዝሞለት በሥራ ላይ እንዲቆይ የተደረገበት ጊዜ፤

ለ) የደመወዝ ክፍያ ሳይቋረጥ በማናቸውም ምክንያት አገልግሎቱ ተቋርጦ የቆየበት ጊዜ፤

PART FOUR
PERIOD OF SERVICE AND RETIREMENT AGE

15. Commencement of Period of Service

1/ The period of service of employee of a private organization shall begin with the date of his employment.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, where an employee of a private organization has pension scheme or provident fund prior to the coming into force of this Proclamation, the pension fund or the provident fund shall be transferred to the Private Organizations Pension Fund, and the service period shall be counted to the extent the pension fund or the provident fund covers the contributions to have been made in accordance with Article 10 of this Proclamation.

3/ The service that an employee of a private organization rendered to public offices shall be counted where his contribution to the Public Servants Pension Scheme is transferred to the Private Organizations Employees Pension Scheme. For the purpose of counting the service, the organ which administers the Public Servants Pension Scheme shall transfer, within one month, the personal records of the employee and the contribution to the Private Organizations Employees Pension Fund.

16. Calculation of Period of Service

1/ Period of service shall be calculated in complete years, months and days.

2/ Without prejudice to the provisions of sub-articles (2) and (3) of Article 15 of this Proclamation, the period of service of an employee of private organization shall include all services rendered to public offices and private organizations covered by the Private Organizations Employees Pension Scheme.

3/ For any employee of private organization the following shall be counted as period of service:

a) period of service beyond retirement age, if lawfully retained in service;

b) period of service which was interrupted without interruption of payment of salary;

ሐ) በየወሩ ደመወዝ እየተከፈለው ሙሉ ጊዜውን በማናቸውም የመንግሥት አካል በሕዝብ ወይም በሠራተኛ ማህበር በተመራጭነት አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፤

መ) በቋሚነት በተቀጠረበት የግል ድርጅት በጊዜያዊነት ሳያቋርጥ በተከታታይ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ፤

ሠ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 3 በንዑስ አንቀጽ /3//ለ/ የተደነገገዉ ቢኖርም በመንግሥት ውሳኔ በዓለም አቀፍ ድርጅት በማገልገል ያሳለፈው ጊዜ፡፡

4/ ለማንኛውም የግል ድርጅት ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚያዝለት የአገልግሎት ዘመን የሚከተለው አይታሰብለትም፡-

ሀ) አገልግሎቱ በሕጉ መሠረት ካልተራ ዘመ በስተቀር የጡረታ መውጫ ዕድ ሜው ከደረሰበት ከሚቀጥለው ወር አንስቶ የሚሰጠው አገልግሎት፤

ለ) ኢትዮጵያ ተዋዋይ ወገን የሆነችበት ማናቸውም ዓለም አቀፍ ስምምነትና የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /3//መ/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በሕጋዊ ፈቃድ የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነ የግል ድርጅት ሠራተኛ የኢትዮጵያን ዜግነት ከማግኘቱ በፊት በመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም በግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት የሰጠው አገልግሎት፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /3/ ከፊደል ተራ (ሐ) እስከ (ሠ) የተመለከተው ጊዜ በአገል ግሎት ዘመንነት ሊታሰብ የሚችለው የግል ድርጅት ሠራተኛው መክፈል ያለበትን የጡረታ መዋጮ የአሰሪውን ድርሻ ጨምሮ ራሱ የከፈለ ወይም እንዲከፈልለት ያደረገ እንደሆነ ነው፡፡

6/ በዚህ አዋጅ ወይም በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት ዳረጎት ተከፍሎት ወይም መዋጮ ተመላሽ ተደርጎለት የነበረ ሰው እንደገና በግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ ዐቅድ በተሸፈነ የግል ድርጅት ሠራተኛነት የተቀጠረ ከሆነና የወሰደውን ዳረጎት ወይም መዋጮ ተመላሽ ከባንክ የማስቀመጫ ወለድ ጋር መልሶ ገቢ ካደረገ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 05/3/ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞው አገልግሎቱ ይታሰብለታል፡፡

c) period of service spent in any public body or trade union as salaried fulltime elected member;

d) period of service rendered to a private organization, without interruption, as a temporary worker if subsequently employed permanently in the same organization;

e) notwithstanding the provision of sub-article (3)(b) of Article 3 of this Proclamation, period of service spent, upon a government decision, in an international organization.

4/ For any employee of a private organization the following shall not be counted as period of service pursuant to this Article :

a) unless lawfully retained, the service he renders as of the first day of the month following that in which he attains retirement age;

b) without prejudice to any international agreement to which Ethiopia is a party and the provision of sub-article (3)(d) of this Article, the service rendered by naturalized Ethiopian in any public office or private organization covered by the Private Organizations Employees Pension Scheme before his naturalization.

5/ Period of service referred to under sub-article (3) from (c) to (e) of this Article shall be counted from as period of service only where the employee pays the contributions by himself including that of the employer or causes the employer to effect payments of same.

6/ Where a person who has received gratuity or to whom reimbursement of pension contribution has been made pursuant to this Proclamation or the Public Servants Pension Proclamation is employed as an employee of a private organization covered by the Private Organizations Employees Pension Scheme, his former service shall, without prejudice to Article 15(3) of this Proclamation, be counted along with the new service; provided, however, that the gratuity or the reimbursed contribution is paid back with interest calculated at bank deposit interest rate.

7/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኤጀንሲው በሚያቀ ርብለት ጥናት መሠረት በከባድ ወይም ለጤንነትና ለሕይወት አስጊ በሆኑ የሥራ መስኮች የተፈጸመ አገልግሎት እስከ አጠ ፌታ እንዲቆጠር ሊወስን ይችላል፡፡

07. <u>የጡረታ መውጫ ዕድሜ</u>

1/ የጡረታ መውጫ ዕድሜ የግል ድርጅት ሠራተኛው ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀጠር በቅድሚያ የመዘገበውን የልደት ዘመን መሠረት በማድረግ % ዓመት ይሆናል፡፡

2/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኤጀንሲው በሚያ ቀርብለት ጥናት መሠረት በልዩ ሁኔታ በሚ ታዩ የሙያ መስኮች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አን ቀጽ /1/ ከተመለከተው በላይ የሆነ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሊወስን ይችላል፡፡

3/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኤጀንሲው በሚያቀ ርብለት ጥናት መሠረት በከባድ ወይም ለጤንነትና ለሕይወት አስጊ በሆኑ የሥራ መስኮች ላይ ለተሰማሩ የግል ድርጅቶች ሠራተኞች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ከተመለከተው ያነሰ የጡረታ መውጫ ዕድሜ ሊወስን ይችላል፡፡

<u>ክፍል አምስት</u>
<u>ስለአገልግሎት ጡረታ አበልና ዳረጎት</u>

08. <u>የአገልግሎት ጡረታ አበል</u>

1/ ቢያንስ 0 ዓመት ያገለገለ የግል ድርጅት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድ ረሱ ከሥራ ሲሰናበት የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡

2/ ቢያንስ ! ዓመት ያገለገለ የግል ድርጅት ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጭ በሆነ ምክንያት አገል ግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡

3/ ቢያንስ !5 ዓመት ያገለገለ የግል ድርጅት ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጭ በሆነ ምክንያት አገልግ ሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሊደርስ አምስት ዓመት ከሚቀረው ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕድሜ ልኩ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል፡፡

7/ On the basis of studies submitted to it by the Agency, the Council of Ministers may decide that period of service spent on hazardous jobs or on jobs involving risk to health and life be counted up to twice the actual period of service.

17. <u>Retirement Age</u>

1/ The retirement age of an employee of a private organization shall be 60 years based on the date of birth registered when he was employed for the first time.

2/ On the basis of studies submitted to it by the Agency, the Council of Minister may determine higher retirement age than the age provided for under sub-article (1) of this Article with respect to professions that may deserve special consideration.

3/ On the basis of studies submitted to it by the Agency, the Council of Ministers may decide retirement age lesser than the age provided for under sub-article (1) of this Article for employees of private organizations working on hazardous jobs or on jobs involving risks to health and life.

<u>PART FIVE</u>
<u>RETIREMENT PENSION AND GRATUITY</u>

18. <u>Retirement Pension</u>

1/ An employee of a private organization who has completed at least 10 years of service and retires upon attaining retirement age shall receive retirement pension for life.

2/ An employee of a private organization who has completed at least 20 years of service and separates from the service by voluntary resignation or for any other causes other than those provided for in this Proclamation shall receive retirement pension for life upon attaining retirement age.

3/ An employee of a private organization who has completed at least 25 years of service and separates from the service by voluntary resignation or for any other causes other than those provided for in this Proclamation shall receive retirement pension for life beginning with five years prior to retirement age.

4/ እድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ መብት መከበሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ ድንጋጌ በዲስፕሊን ጉድለት ምክንያት አገልግሎቱ ለተቋረጠ የግል ድርጅት ሠራተኛ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ወይም /3/ ወይም /4/ መሠረት አገልግሎቱ የተቋረጠ የግል ድርጅት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው ሳይደርስ በጤና ጉድለት ምክንያት ለሥራ ብቁ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ይኸው ከተረጋገጠበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል፡፡ የሞተ እንደሆነም ከሞተበት ጊዜ ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ ለተተኪዎች አበል ይከፈላል፡፡

09. <u>የአገልግሎት ጡረታ አበል መጠን</u>

1/ ለማንኛውም 0 ዓመት ላገለገለ የግል ድር ጅት ሠራተኛ የሚከፈለው የአገልግሎት ጡረታ አበል መጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ይከፈለው የነበረው አማካይ ደመወዝ "በመቶ ሆኖ ከ0 ዓመት በላይ ለፈጸመው ለእያንዳንዱ ዓመት አገልግሎት 1.25በመቶ ተጨምሮ ይታሰባል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወሰነው የአበል መጠን የግል ድርጅት ሠራተኛው በመጨረሻ ባገለገለባቸው ሦስት ዓመታት ውስጥ ይከፈለው ከነበረው አማካይ ደመወዝ &በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

!. <u>የአገልግሎት ዳረጎት</u>

ከ0 ዓመት ያነሰ አገልግሎት የፈጸመ የግል ድርጅት ሠራተኛ የጡረታ መውጫ ዕድሜው በመድረሱ ከሥራ ሲሰናበት የአገልግሎት ዳረጎት ይከፈለዋል፡፡

!1. <u>የአገልግሎት ዳረጎት መጠን</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ! መሠረት የሚከፈለው ዳረጎት የግል ድርጅት ሠራተኛው ከሥራ ከተሰናበተበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው የ1.25 ወር ደመወዝ በአገለገለበት ዓመት ቁጥር ተባዝቶ ይታሰባል፡፡

4/ Without prejudice to the entitlement of pension right up on attainment of retirement age the provisions of sub-article (3) of this Article shall not be applicable to an employee of a private organization who separates from the service on grounds of disciplinary measures.

5/ Where it is ascertained that an employee of a private organization who has separated from service in accordance with sub-article (2) or (3) or (4) of this Article becomes incapable of fulfilling the medical conditions of service due to health problems prior to attaining the retirement age, he shall receive retirement pension for life starting with the month following such ascertainment; in case he dies, his survivors shall be paid benefits starting with the month following his death.

19. <u>Amount of Retirement Pension</u>

1/ The retirement pension due to any employee of private organization shall be 30% of his average salary of the last three years preceding retirement and shall be increased by 1.25% for each year of service beyond 10 years.

2/ The retirement pension to be paid pursuant to sub-article (1) of this Article may not exceed 70% of the average salary of the employee of private organization for the last three years preceding retirement.

20. <u>Retirement Gratuity</u>

An employee of private organization who has not completed 10 year of service and retires on attaining retirement age shall receive gratuity.

21. <u>Amount of Retirement Gratuity</u>

The gratuity payable in accordance with Article 20 of this Proclamation shall be his salary for 1.25 month preceding retirement multiplied by the number of years of service.

ክፍል ስድስት
ስለጤና ጉድለት ጡረታ አበልና ዳረጎት

!2. የጤና ጉድለት ጡረታ አበል

ቢያንስ 0 ዓመት ያገለገለ የግል ድርጅት ሠራተኛ በጤና ጉድለት ምክንያት ደመወዝ የሚያስገኝ ማናቸውንም ሥራ መሥራት የማይችል በመሆኑ ከሥራ ሲሰናበት የጤና ጉድለት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል።

!3. የጤና ጉድለት ጡረታ አበል መጠን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ !2 መሠረት የሚከፈለው የጤና ጉድለት ጡረታ አበል በአንቀጽ 09 መሠረት ይታሰባል።

!4. የጤና ጉድለት ዳረጎት

ከ0 ዓመት ያነሰ አገልግሎት የፈጸመ የግል ድርጅት ሠራተኛ በጤና ጉድለት ምክንያት ለሥራ ብቁ ባለመሆኑ ከሥራ ሲሰናበት የጤና ጉድለት ዳረጎት ይከፈለዋል።

!5. የጤና ጉድለት ዳረጎት መጠን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ !4 መሠረት የሚከፈለው ዳረጎት በአንቀጽ !1 መሠረት ይታሰባል።

!6. ስለጡረታ መዋጮ ተመላሽ

1/ አንድ የግል ድርጅት ሠራተኛ፡-

ሀ) ከ0 ዓመት ያላነሰና ! ዓመት ያልሞላ አገልግሎት ፈጽሞ በራሱ ፈቃድ ሥራውን ከለቀቀ፤ ወይም

ለ) ከ! ዓመት ያነሰ አገልግሎት ፈጽሞ በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት ከሥራ ከተሰናበተ፤

የአሠሪውን ድርሻ ሳይጨምር ሠራተኛው ራሱ ባዋጣው መጠን ብቻ የጡረታ መዋጮ ይመለስለታል።

2/ ከ0 ዓመት ያነሰ አገልግሎት ፈጽሞ በራሱ ፈቃድ ሥራውን ከለቀቀ ምንም ዓይነት ክፍያ አያገኝም።

PART SIX
INVALIDITY PENSION AND GRATUITY

22. Invalidity Pension

Employee of private organization who has completed at least 10 years of service and separates from service due to health problems preventing him from engaging in any remunerated work shall receive invalidity pension for life.

23. Amount of Invalidity Pension

The invalidity pension payable in accordance with Article 22 of this Proclamation shall be calculated as provided under Article 19 hereof.

24. Invalidity Gratuity

An employee of private organization who has not completed 10 years of service and separates from service on becoming unfit for service due to health problems shall receive invalidity gratuity.

25. Amount of Invalidity Gratuity

The gratuity payable in accordance with Article 24 of this proclamation shall be calculated as provided under Article 21 hereof.

26. Reimbursement of Pension Contribution

1/ An employee of private organization who separates from service:

a) due to resignation after completing 10 years, but prior to completing 20 years of service; or

b) for any other cause other than those specified by this Proclamation prior to 20 years of service.

shall be paid an amount equal to the total pension contributions made by him excluding contributions of the employer.

2/ An employee of private organization who separates from work due to resignation prior to completing 10 years of service shall not be entitled to any benefit.

ክፍል ሰባት
ስለጉዳት ጡረታ አበልና ዳረጎት

!7. ትርጓሜ

1/ "በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት" ማለት በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው።

2/ "በሥራ ላይ የሚደርስ አደጋ" ማለት የግል ድርጅት ሠራተኛው መደበኛ ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ወይም ከሥራ ጋር በተያያዘ ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ የተፈጥሮ ተግባር ላይ በድንገት የሚደርስ ጉዳት ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

ሀ) የግል ድርጅት ሠራተኛው ከመደበኛ ሥራው ወይም መደበኛ የሥራ ቦታው ወይም ሰዓት ውጭ ስልጣኑ በሚፈቅድለት የሥራ ኃላፊ የተሰጠውን ትዕዛዝ በመፈጸም ላይ እያለ የደረሰን ጉዳት፤

ለ) ሥልጣኑ በሚፈቅድለት የሥራ ኃላፊ የተሰጠው ትዕዛዝ ባይኖርም የግል ድርጅት ሠራተኛው በግል ድርጅቱ ውስጥ የደረሰን ድንገተኛ አደጋ ወይም ጥፋት ለመከላከል በሥራ ሰዓት ወይም ከሥራ ሰዓት ውጭ በሚፈጽመው ተግባር ምክንያት የደረሰን ጉዳት፤

ሐ) የግል ድርጅት ሠራተኛው ወደ ሥራ ቦታው ወይም ከሥራ ቦታው አሠሪው ለሠራተኞች አገልግሎት እንዲሰጥ በመደበው የመንገገጥ አገልግሎት ወይም አሠሪው ለዚህ ተግባር በተከራየውና በግልጽ በመደበው የመንገገጥ አገልግሎት በመንገዘ ላይ በነበረበት ጊዜ የደረሰን ጉዳት፤

መ) የግል ድርጅት ሠራተኛው ከሥራው ጋር በተያያዘ ግዴታ የተነሣ ከሥራው በፊት ወይም በኋላ ወይም ሥራው ለጊዜው ተቋርጦ በነበረበት ጊዜ በሥራ ቦታው ወይም በግል ድርጅቱ ግቢ ውስጥ በመገኘት የደረሰበትን ማንኛውንም ጉዳት፤

ሠ) የግል ድርጅት ሠራተኛው ሥራውን በማከናወን ላይ ባለበት ጊዜ በአሠሪው ወይም በሦስተኛ ወገን ድርጊት ምክንያት የደረሰበትን ጉዳት።

PART SEVEN
EMPLOYMENT INJURY PENSION AND GRATUITY

27. Definitions

1/ "employment injury" means an occupational accident or occupational disease.

2/ "occupational accident" means any organic injury or functional disorder suddenly sustained by an employee during or in connection with the performance of his work, and shall include the following:

a) any injury sustained by an employee of private organization while carrying out orders given by a competent authority outside of his regular work or working place or working hours;

b) any injury sustained by an employee during or outside of working hours while attempting to protect the private organization from accident or destruction irrespective of an order given by a competent authority;

c) any injury sustained by an employee while he is proceeding to or from his place of work in a transport service vehicle provided by the private organization which is available for the common use of its employees or in a vehicle hired and expressly destined by the organization for the same purpose;

d) any injury sustained by an employee before or after his work or during any interruption of work, if he is present in the work place or the premises of the private organization by reason of his duties in connection with this work;

e) any injury sustained by an employee as a result of an action of the private organization or a third person during the performance of his work.

3/ "በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ" ማለት የግል ድርጅት ሠራተኛው ከሚሠራው የሥራ ዓይነት ወይም ሥራውን ከሚያከናውንበት አካባቢ የተነሣ በሽታውን ለሚያስከትሉ ሁኔታዎች ተጋልጦ በመቆየቱ ምክንያት የደረሰ የጤና መታወክ ሲሆን ሥራውን በሚያከናውንበት ቦታ የሚዛመቱና የሚይዙ ነዋሪ ወይም ተላላፊ በሽታዎችን አይጨምርም፡፡

4/ "መደበኛ ሥራ" ማለት የግል ድርጅት ሠራ ተኛው በተሰጠው ኃላፊነት ወይም የሥራ ውል መሠረት የሚያከናውነው ተግባር ነው፡፡

5/ "መደበኛ የሥራ ቦታ" ማለት የግል ድርጅት ሠራተኛው የግል ድርጅቱን ሥራ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የሚያከናውንበት ሥፍራ ነው፡፡

!8. <u>በራስ ላይ ጉዳት ስለማድረስ</u>

በዚህ አዋጅ አንቀጽ !7 የተመለከተው ተቀባይነት የሚኖረው የግል ድርጅት ሠራተኛው ጉዳቱ እንዲደርስበት ሆነ ብሎ ያላደረገው ሲሆን ነው፡፡ በተለይም ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የደረሰ ጉዳት የግል ድርጅት ሠራተኛው በራሱ ላይ ሆን ብሎ ያደረሰው ጉዳት ሆኖ ይቆጠራል፡-

1/ በአሠሪው አስቀድሞ በግልጽ የተሰጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎች መጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን መተላለፍ፤ ወይም

2/ አካሉን ወይም አእምሮውን በሚገባ ለመቆ ጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ ዕጽ ሰክሮ በሥራ ላይ በመገኘት፤ የደረሰ ጉዳት፡፡

!9. <u>በሥራ ምክንያት የሚመጣ በሽታና የአካል ጉዳት መጠን ሠንጠረዥ</u>

1/ ኤጀንሲው አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም፡-

ሀ) የአካል ጉዳት መጠን፤

ለ) እያንዳንዱን በሥራ ምክንያት የሚ መጣ በሽታን በሚመለከት፡-

/1/ የበሽታውን ምልክቶች፤

3/ "occupational disease" means any pathological condition of an employee of private organization which arises as a consequence of being exposed to the agent that cause the disease for a certain period prior to the date in which the disease became evident due to the kind of work he performs or because of the surrounding in which he works; provided, however, that it does not include endemic or epidemic diseases which are prevalent and contracted in the area where the work is done.

4/ "regular work" means a work performed by an employee of private organization pursuant to his assignments or contract of employment.

5/ "regular place of work" means a place where an employee of private organization performs his duties for definite or indefinite period.

28. <u>Self Inflicted Injury</u>

The provisions of Article 27 of this Proclamation shall apply only where the employee has not inflicted the injury upon himself intentionally. Any injury resulting from, in particular, the following acts shall be deemed to be intentionally caused by the employee of private organization:

1/ non-observance of safety instructions or preventive rules specifically issued by the private organization; or

2/ reporting to work in a state of intoxication that prevents him from properly regulating his conduct or understanding.

29. <u>Schedule of Occupational Diseases and Degrees of Incapacity</u>

1/ The Agency shall, in consultation with the appropriate organ and by directives, issue a schedule that lists:

a) the degrees of incapacity;

b) with respect to each occupational disease:

(1) the symptoms;

(2) ለበሽታው መነሻ ይሆናል ተብሎ የሚታመነውን የሥራ ዓይነት ወይም አካባቢ፤

(3) በሽታውን ለሚያሲዘው የሥራ ሁኔታ ለመጋለጥ የሚያስፈልገውን አነስተኛ ጊዜ፤

የያዘ ዝርዝር ሠንጠረዥ በመመሪያ ያወጣል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጣው ሠንጠረዥ እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው ይሻሻላል።

(2) the kind of work or surrounding that gives rise to the disease;

(3) the minimum duration of exposure to the agent causing the disease.

2/ The schedule issued in accordance with sub-article (1) of this Article shall be revised periodically as necessary.

". ግምት

1/ ከሥራው ቦታ ወይም ከሥራው ዓይነት ጋር የተያያዘ በሠንጠረዡ ውስጥ የተመለከተ በሽታ በተጠቀሰው የሥራ ቦታ ወይም የሥራ ዓይነት ላይ የተሰማራን የግል ድርጅት ሠራተኛ የያዘው እንደሆነ በሽታው በሥራ ምክንያት እንደመጣ ይቆጠራል።

2/ በሥራ ምክንያት በሚመጣ በሽታ ተይዞ የዳነ የግል ድርጅት ሠራተኛ በሰንጠረዡ ውስጥ በበሽታው አንጻር በተመለከተው የሥራ ዓይነት ላይ ተመድቦ መሥራት በመቀጠሉ በዚያው በሽታ እንደገና ቢያዝ አዲስ በሽታ እንደያዘው ይቆጠራል።

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ !7 ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው ቢኖርም በመደበኛ ሥራው ምክንያት ተላላፊ ወይም ነዋሪ በሽታዎችን በማጥፋት ላይ የተሰማራ የግል ድርጅት ሠራተኛ በዚሁ በሽታ ከተያዘ በሥራ ምክንያት የመጣ በሽታ እንደያዘው ይቆጠራል።

30. Presumption

1/ Where a disease listed in the schedule is contracted by an employee of private organization engaged in the corresponding work place or kind of work, it shall be presumed an occupational disease.

2/ Where an employee of private organization who had recovered from an occupational disease is re-infected due to continued placement in the occupation corresponding to the disease listed in the schedule, he shall be presumed to have contracted the occupational disease afresh.

3/ Notwithstanding sub-article (3) of Article 27 of this Proclamation where an employee of a private organization engaged in the eradication of endemic or epidemic disease contracts same, it shall be presumed an occupational disease.

"1. ማስረጃ ማቅረብ ስለመቻሉ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ !9 መሠረት በሚወጣው ሠንጠረዥ ውስጥ ያልተመለከተ በሽታ በሥራ ምክንያት የመጣ መሆኑን እንሁም በሠንጠረዡ ውስጥ የተመለከተ በሽታ በአንጻሩ ከተመለከቱት ምልክቶች በተለየ ሁኔታ የተከሰተ መሆኑን ለማረጋገጥ ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል።

31. Admissibility of Evidence

Production of evidence may be permitted to proof that a disease not listed in the schedule issued under Article 29 of this Proclamation is of occupational origin, and that a disease listed in the schedule has been manifested in different symptoms from those indicated therein.

"2. **አደጋን ስለማስታወቅ**

አንድ የግል ድርጅት ሠራተኛ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ የግል ድርጅቱ አደጋው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ባሉት " ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለኤጀንሲው ማስታወቅ አለበት። ይህ ባለመደረጉ በግል ድርጅት ሠራተኛው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የግል ድርጅቱ ኃላፊ ይሆናል።

"3. **ስለአካል ጉዳት መጠን አወሳሰን**

1/ በሥራ ምክንያት የሚመጣ የጉዳት መጠን የሚወሰነው ሥልጣን በተሰጠው የህክምና ቦርድ ነው።

2/ ማንኛውም የህክምና ቦርድ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት መጠንን የሚተምነው በዚህ አዋጅ አንቀጽ !9 በተመለከተው ሠንጠረዥ መሠረት ይሆናል።

3/ ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በአንድ የህክምና ቦርድ የተሰጠ ውሳኔ በሌላ ህክምና ቦርድ እንደገና እንዲታይ ሊያደርግ ይችላል።

"4. **የጉዳት አበል**

በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ከ0በመቶ ያላነሰ ሊድን የማይችል ጉዳት ለደረሰበት የግል ድርጅት ሠራተኛ እንደሁኔታዉ የጉዳት ጡረታ አበል ወይም የጉዳት ዳረጎት ይከፈላል።

"5. **የጉዳት ጡረታ አበል**

አንድ የግል ድርጅት ሠራተኛ በሥራ ላይ በሚደርስ ጉዳት ምክንያት ከ0በመቶ ያላነሰ ሊድን የማይችል ጉዳት ደርሶበት ደመወዝ የሚያስገኝ ማናቸውንም ሥራ መሥራት የማይችል በመ ሆኑ ከሥራ ሲሰናበት የጉዳት ጡረታ አበል እስከ ዕድሜ ልኩ ይከፈለዋል።

"6. **የጉዳት ጡረታ አበል መጠን**

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ "5 መሠረት የሚከፈለው የጉዳት የጡረታ አበል መጠን የግል ድርጅት ሠራተኛው ጉዳቱ ከደረሰበት ወር በፊት ያገኝ ከነበረው መደበኛ የወር ደመወዝ #7በመቶ ይሆናል።

32. Notification of Accident

Where an employee of private organization sustains occupational injury, the private organization shall notify, in writing, the occurrence of same to the Agency within 30 days of such occurrence. Failure to do so shall make the private organization liable for the injury sustained by the employee.

33. Assessment of Employment Injury

1/ The extent of employment injury sustained by an employee of private organization shall be assessed by authorized medical board.

2/ Any medical board shall assess the extent of employment injury based on the schedule issued pursuant to Article 29 of this Proclamation.

3/ When it deems necessary, the Agency may refer the assessment to another medical board for further evaluation.

34. Incapacity Benefit

Incapacity pension for life or incapacity gratuity shall be paid, as the case may be, to an employee of private organization who sustains employment injury of not less than 10%.

35. Incapacity Pension

An employee of private organization who sustains employment injury of not less than 10% and separates from work due to permanent incapacity that prevents him from engaging in any remunerated work shall receive incapacity pension for life.

36. Amount of Incapacity Pension

1/ The amount of incapacity pension to be paid in accordance with Article 35 of this Proclamation shall be 47% of his salary which he was receiving during the month prior to the occurrence of the injury.

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አበል ሊከፈለው የሚችል የግል ድርጅት ሠራተኛ በአገልግሎቱ ሊያገኝ የሚችለው አበል በጉዳት ሊያገኝ ከሚችለው የበለጠ ከሆነ የአገልግሎት ጡረታ አበል ይከፈለዋል፡፡

"7. **የጉዳት ዳረጎት**

1/ አንድ የግል ድርጅት ሠራተኛ ከ0በመቶ ያላነሰ ከሥራ የመጣ ጉዳት ደርሶበት ሥራ ለመሥራት የሚችል ከሆነ የጉዳት ዳረጎት ለአንድ ጊዜ ይከፈለዋል፡፡

2/ የግል ድርጅት ሠራተኛው አግባብ ባለው ሕግ ወይም ኅብረት ስምምነት መሠረት በአሠሪው የጉዳት ካሣ ወይም የመድን ክፍያ የሚያገኝ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው የጉዳት ዳረጎት አይከፈ ለውም፡፡

"8. **የጉዳት ዳረጎት መጠን**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ "7 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የጉዳት ዳረጎት መጠን የግል ድርጅት ሠራተኛው ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት ይከፈለው የነበረው መደበኛ የወር ደመወዙ #7 በመቶ በ% ተባዝቶ የሚገኘው ሂሣብ በሠራተኛው ላይ በደረሰው ጉዳት መቶኛ ተባዝቶ ነው፡፡

ክፍል ስምንት
የተተኪዎች ጡረታ አበልና ዳረጎት

"9. **ጠ ቅ ላ ላ**

1/ ማንኛውም የግል ድርጅት ሠራተኛ፡-

ሀ) የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ወይም የጉዳት ጡረታ አበል በመከፈል ላይ እያለ፤ ወይም

ለ) ቢያንስ 0 ዓመት አገልግሎ በሥራ ላይ እያለ፤ ወይም

ሐ) በሥራ ላይ በደረሰበት ጉዳት ምክንያት፤ ከሞተ ለተተኪዎቹ የጡረታ አበል ይከፈላል፡፡

2/ ከአሥር ዓመት ያነሰ አገልግሎት ያለው ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ ከሞተ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ /ሀ/ እና /ለ/ ለተመ ለከቱት ተተኪዎች ዳረጎት ይከፈላቸዋል፡፡

2/ If the retirement pension to which the employee of private organization is entitled is higher than the incapacity pension to be paid pursuant to sub-article (1) of this Article, he shall receive the retirement pension.

37. **Incapacity Gratuity**

1/ An employee of private organization who sustains employment injury of not less than 10% without loss of capacity to work shall receive incapacity gratuity in the form of lump sum.

2/ If the employee of private organization is entitled to compensation for damage in accordance with the appropriate law or collective agreement from the employer or insurance benefit, he shall not receive the incapacity gratuity to be paid pursuant to sub-article (1) of this Article.

38. **Amount of Incapacity Gratuity**

The amount of incapacity gratuity payable in accordance with sub-article (1) of Article 37 of this Proclamation shall be equal to 47% of the monthly salary of the employee of private organization which he was receiving during the month preceding the occurrence of the injury multiplied by 60 and the percentage of injury sustained.

PART EIGHT
SURVIVORS PENSION AND GRATUITY

39. **General**

1/ Pension shall be paid to the survivors of an employee of private organization who dies:

a) while receiving retirement or invalidity or incapacity pension; or

b) while in service upon completing at least 10 years of service; or

c) due to employment injury.

2/ If an employee of private organization who has not completed 10 years of service dies before he separates from the service, his survivors falling under sub-article (3)(a) and (b) of this Article shall receive gratuity.

3/ የሟች ተተኪዎች የሚባሉት የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ) ሚስት ወይም ባል፤

ለ) ከ08 ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ልጆች ወይም አካል ጉዳተኛ ወይም አዕምሮ በሽተኛ ልጅ ሲሆን ዕድሜው ከ!1 ዓመት በታች የሆነ፤

ሐ) ልጃቸው ከመሞቱ በፊት ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በሟች ድጋፍ ይተዳደሩ የነበሩ ወላጆች፡፡

#. የሟች ሚስት ወይም ባል ጡረታ አበል

1/ ለሟች ሚስት ወይም ባል የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል $በመቶ ይሆናል፡፡

2/ የሟች ሚስት ወይም ባል የጡረታ አበል ተወስኖ በመቀበል ላይ እያለች ወይም እያለ ጋብቻ ከፈጸመች ወይም ከፈጸመ፡-

ሀ) ሚስት ዕድሜዋ ከ#5 ዓመት በታች ከሆነ፤ ወይም

ለ) ባል እድሜው ከ$ ዓመት በታች ከሆነ፤ ጋብቻ ከተፈጸመበት ቀን ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ በመከፈል ላይ ያለው የጡረታ አበል ይቋረጣል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት መቋረጥ የሚገባውን የጡረታ አበል የተቀበለች ወይም የተቀበለ የሟች ሚስት ወይም ባል መልሶ የመክፈል ግዴታ አለባት ወይም አለበት፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ድንጋጌዎች በአካል ጉዳተኛ ሚስት ወይም ባል ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

5/ ለሟች ሚስት ወይም ባል በዚህ አንቀጽ መሠረት ከአንድ በላይ የጡረታ አበል የሚከፈልበት ሁኔታ ሲያጋጥም አንዱና የሚበልጠው ብቻ ይከፈላል፡፡

#1. የሟች ልጅ ጡረታ አበል

1/ ለሟች ልጅ የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል !በመቶ ይሆናል፡፡

3/ The following shall be considered as survivors:

a) a widow or widower;

b) children of the deceased who are under the age of 18 years or in case of disabled child or child with mental health problem, under the age of 21 years;

c) parents who were wholly or mainly supported by the deceased preceding his death.

40. Widow's or Widower's Pension

1/ The amount of pension payable to a widow or widower shall be 50% of the pension to which the deceased was or would have been entitled.

2/ Widow's or widower's pension shall be discontinued from the beginning of the month following remarriage where:

a) the age of widow is less than 45 years; or

b) the age of widower is less than 50 years.

3/ A widow or widower shall return the pension received in violation of sub-article (2) of this Article.

4/ The provisions of sub-articles (2) and (3) of this Article shall not be applicable to disabled widow or widower.

5/ Where a widow or widower is entitled to more than one pensions in accordance with the provisions of this Article, the one that is higher shall be paid.

41. Surviving Child's Pension

1/ The amount of pension payable to surviving child shall be 20% of the pension to which the deceased was or would have been entitled.

2/ ሁለቱም ወላጆቹ ለሞቱበት ልጅ በዚህ አን ቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የጡረታ አበል "በመቶ ይሆናል።

3/ የጡረታ አበል የሚከፈላቸው ወይም ሊከፈ ላቸው ይችሉ የነበሩ ሁለቱም ወላጆቹ የሞ ቱበት ልጅ ከእያንዳንዳቸው አበል !በመቶ ይከፈለዋል፤ ሆኖም የጡረታ አበሉ ድምር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ሊከፈል ከሚችለው ያነሰ አይሆንም።

#2. <u>የወላጅ ጡረታ አበል</u>

ለሟች ወላጆች ለእያንዳንዳቸው የሚከፈለው የጡረታ አበል ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል የነበረው የጡረታ አበል 05በመቶ ይሆናል። ሆኖም ከወላጆች ሌላ ተተኪ ከሌለ !በመቶ ይሆናል።

#3. <u>የተተኪዎች ዳረጎት</u>

በዚህ አዋጅ አንቀፅ "9 /2/ ለተመለከቱት ተተኪዎች የሚከፈለው የዳረጎት መጠን ለሟች በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈለው ይገባ ከነበረው ዳረጎት እንደአግባቡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ #(1) ወይም አንቀፅ #1 በተወሰነው መቶኛ ተባዝቶ ይታሰባል።

#4. <u>የተተኪዎች አበል ገደብ</u>

1/ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ # እስከ አንቀፅ #3 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ለተተኪዎች የሚከፈለው አበል ድምር ሟች ያገኝ ወይም ሊያገኝ ይችል ከነበረው አበል 1)በመቶ /መቶ በመቶ/ ሊበልጥ አይችልም። ከተጠቀሰው መጠን በልጦ ከተገኘ ግን ከእያንዳንዱ ተተኪ አበል ላይ ተመጣጣኝ ቅናሽ ይደረጋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተተኪዎች ጡረታ አበል ከተስተካከለ በኋላ የተተኪዎች ብዛት ከቀነሰ የአበሉ መጠን እንደገና ይስተካከላል።

<u>ክፍል ዘጠኝ</u>
<u>አበልን የሚመለከቱ የወል ድንጋጌዎች</u>

#5. <u>ስለዝቅተኛ የጡረታ አበል መጠንና የአበል መሻሻል</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኤጀንሲው በሚያቀር በው ጥናት መሠረት በየአምስት ዓመቱ ዝቅተኛ ወርሃዊ የጡረታ አበል መጠንና የጡረታ አበል ማስተካከያ ያደርጋል።

2/ If both parents are dead, the amount of pension payable to surviving child in accordance with sub-article (1) of this Article shall be 30%.

3/ If both parents of a child are dead, he shall receive 20% of the pension to which each of the deceased parent was or would have been entitled; provided, however, that the sum of such pensions shall not be less than the amount payable in accordance with sub-article (2) of this Article.

42. <u>Parent's Pension</u>

The amount of pension payable to each parent shall be 15% of the pension to which the deceased was or would have been entitled. If there are no survivors other than the parents, the pension shall be 20%.

43. <u>Survivors' Gratuity</u>

The amount of gratuity payable to the survivors referred to under Article 39 (2) of this Proclamation shall be the amount of gratuity to which the deceased would have been entitled and shall be calculated in accordance with the percentage specified in Article 40(1) or Article 41 of this Proclamation, as the case may be.

44. <u>Limit of Survivors' Benefits</u>

1/ The total amount of benefits payable to survivors in accordance with the provisions from Article 40 to Article 43 of this Proclamation shall not exceed 100% (hundred percent) of the benefit to which the deceased was or would have been entitled. In the case of excess sum, each survivor's share shall be proportionately reduced to adjust until the total comes down to100%.

2/ If the number of survivors is reduced subsequent to adjustment under sub-article (1) of this Article, further adjustment of the amount of benefits shall be made accordingly.

<u>PART NINE</u>
<u>GENERAL PROVISIONS RELATING TO BENEFITS</u>

45. <u>Minimum Pension and Pension Adjustment</u>

On the basis of studies submitted to it by the Agency, the Council of Ministers may adjust the minimum monthly pension benefit and pension every five years.

#6. <u>የጡረታ አበል አከፋፈልና የመክፈያ ጊዜ</u>

1/ የጡረታ አበል የሚከፈለው በየወሩ ይሆናል፡፡

2/ የአገልግሎት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የግል ድርጅት ሠራተኛው በዕድሜ ለጡረታ ብቁ ከሆነበት ቀጥሎ ካለው ወር መጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፡፡

3/ የጤና ጉድለት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የግል ድርጅት ሠራተኛው በጤና ጉድለት ምክንያት መሥራት የማይችል መሆኑ በሕክምና ቦርድ ከተረጋገጠበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፡፡

4/ የጉዳት ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው የግል ድርጅት ሠራተኛው በጉዳት ምክንያት መሥራት የማይችል መሆኑ በሕክምና ቦርድ ከተረጋገጠበት ቀጥሎ ካለው ወር የመጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፡፡

5/ የተተኪዎች ጡረታ አበል መታሰብ የሚጀምረው ባለመብቱ ከሞተበት ቀጥሎ ካለው ወር መጀመሪያ ቀን አንስቶ ነው፡፡

#7. <u>የዳረጎት አከፋፈልና የመክፈያ ጊዜ</u>

1/ ማንኛውም ዳረጎት የሚከፈለው በአንድ ጊዜ ነው፡፡

2/ የአገልግሎት ወይም የጤና ጉድለት ዳረጎት ተከፋይ የሚሆነው የግል ድርጅት ሠራተኛው ከሥራ ከተሰናበተበት ቀጥሎ ባለው ወር የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ነው፡፡

3/ የጉዳት ዳረጎት ተከፋይ የሚሆነው የግል ድርጅት ሠራተኛው ላይ ጉዳት ስለመድረሱና መጠኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

#8. <u>የይርጋ ጊዜ</u>

1/ ማንኛውም የውዝፍ ጡረታ አበል ወይም የዳረጎት ክፍያ ጥያቄ ከሦስት ዓመት በኋላ በይርጋ ይታገዳል፡፡

2/ የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ጥያቄ የግል ድርጅት ሠራተኛው የጡረታ መውጫ ዕድሜ ከሞላ ወይም ከሞተ ከሦስት ዓመት በኋላ በይርጋ ይታገዳል፡፡

3/ የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ መጠቀም ከሚቻልበት ቀጥሎ ካለው ቀን አንስቶ ነው፡፡

46. <u>Mode and Period of Payment of Pension</u>

1/ Payment of pension shall be effected monthly.

2/ Retirement pension shall commence to accrue as of the first day of the month following that in which the employee of private organization retires.

3/ Invalidity pension shall commence to accrue as of the first day of the month following that in which the invalidity of the employee of private organization is ascertained by medical board.

4/ Incapacity pension shall commence to accrue as of the first day of the month following that in which the permanent total incapacity sustained by the employee of private organization is ascertained by medical board.

5/ Survivor's pension shall commence to accrue as of the first day of the month following that in which the beneficiary dies.

47. <u>Mode and Period of Payment of Gratuity</u>

1/ Payment of any gratuity shall be effected in lump sum at once.

2/ Retirement or invalidity gratuity shall be payable beginning with the first day of the month following that in which the employee of private organization separates from the service.

3/ Incapacity gratuity shall be payable beginning with the day where evidence ascertaining the injury and its degree is submitted.

48. <u>Period of Limitation</u>

1/ Any claim for payment of arrears of pension or payment of gratuity shall be barred by limitation after 3 years.

2/ A claim for reimbursement of pension contribution shall be barred by limitation after 3 years from the date in which the employee of private organization attains retirement age or dies.

3/ The period of limitation shall begin to run from the day following that in which the right may be exercised.

4/ በሚከተሉት ምክንያቶች የባከነ ጊዜ ለይርጋ አቆጣጠር አይታሰብም፡-

ሀ) ባለመብትነትን ለማረጋገጥ የተጀመረ የፍርድ ቤት ሥርዓት እስከሚጠናቀቅ የወሰደው ጊዜ፤

ለ) ማንኛውም የግል ድርጅት መረጃ የማስተላለፍ ግዴታውን በወቅቱ ባለመወጣቱ ያለፈው ጊዜ፤

ሐ) ኤጀንሲው የቀረበለትን የክፍያ ጥያቄ መርምሮ ለመወሰን የወሰደው ጊዜ፡፡

#9. <u>አበል የማግኘት መብትን ማስተላለፍ ስላለመቻሉ</u>

አበል የማግኘት መብት የዕዳ መያዣ ሊደረግ ወይም በውርስም ሆነ በሌላ በማናቸውም መንገድ ሊተላለፍ አይችልም፡፡

$. <u>ስለአበል በሕግ መከበር</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ አበል፡-

1/ ለመንግሥት ገቢ የሚሆን መቀጮ፤ ግብር ወይም ቀረጥ ለመክፈል፤ ወይም

2/ አግባብ ባለዉ ሕግ መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታን ለመወጣት፤

በፍርድ ቤት ካልታዘዘ በስተቀር በሌላ ዕዳ ምክን ያት አይከበርም፡፡

<u>ክፍል አሥር</u>
<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

$1. <u>የመብቶች ግንኙነት</u>

1/ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያለ ባለመብት በዚህ አዋጅ በሚሸፈን የግል ድርጅት በቋሚ ነት ከተቀጠረና ለጡረታ መውጫ ዕድሜ ያልደረሰ ከሆነ አዲሱ አገልግሎት ከቀድሞ አገልግሎቱ ጋር ተደምሮ ይታሰብለታል፡፡ ሆኖም እንደገና የታሰበው አበል ከቀድሞው አበል ያነሰ ከሆነ የቀድሞውን አበል የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ ክፍል ስምንት የተደነገገው እንደተ ጠበቀ ሆኖ አንድ ባለመብት በዚህ አዋጅ መሠረት ከአንድ በላይ የጡረታ አበል የሚያገኝበት ሁኔታ ሲያጋጥም ሊከፈል የሚገባው የአበል መጠን ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

4/ The period of limitation shall not include the following:

a) period lapsed due to a court process started to establish right;

b) period lapsed due to failure of a private organization to submit evidentiary documents on time;

c) periods necessary for the decision of benefit entitlement by the Agency.

49. <u>None-Transferability of Benefit Entitlement</u>

The right to receive benefits shall not be pledged or transferred by inheritance or any other means.

50. <u>Attachment of Benefits</u>

Benefits payable in accordance with this Proclamation shall not be attached in relation to any debts unless ordered by a court in respect of:

1/ public fines, taxes or charges; or

2/ fulfillment of the obligation to supply maintenance in accordance with the relevant law.

<u>PART TEN</u>
<u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

51. <u>Relationship Between Entitlements</u>

1/ If an employee of private organization who receives retirement benefit is employed as a permanent employee in a private organization covered by this Proclamation and has not reached the retirement age, his new service shall be added to his previous service; provided, however, that if the retirement pension based on the accumulated service is less than the previous one, he shall have the right to receive the previous retirement pension.

2/ Without prejudice to the provisions of Part Eight of this Proclamation, if a beneficiary is entitled to more than one benefit, the amount of benefit to be paid shall be decided in accordance with the directive to be issued by the Agency.

3/ ይህ አዋጅ ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ወደ ግል ጡረታ ፈንድ ከተዛወረ የጡረታ ዐቅድ የዘለቄታ ጡረታ አበል በመቀበል ላይ የሚገኝ ከሥራ የተሰናበተ የግል ድርጅት ሠራተኛ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ሲከፈለው በነበረው መጠን የጡረታ አበል መቀበሉን ይቀጥላል፡፡

$2. መረጃ የመስጠትና የመተባበር ግዴታ

1/ ማንኛውም የግል ድርጅት ከኤጀንሲው በሚ ተላለፈው መመሪያ መሠረት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ እያንዳንዱን የግል ድርጅት ሠራተኛ የሚመለከቱ መረጃዎችና ማስረጃዎች ማሰባሰብ፣ ማጠናቀር፣ ማደራ ጀትና በኤጀንሲው በሚወሰነው ጊዜና ቅጽ መሠረት ለኤጀንሲው የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡

2/ ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል እንዲቻል ማንኛውም ሰው የጽሁፍ ማስረጃ እንዲልክ ወይም ቀርቦ አስተያየትና መረጃ እንዲሰጥ በኤጀ ንሲው ሲጠየቅ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

3/ የሚመለከታቸው አካላት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 01 ንዑስ አንቀጽ (4) በሚሰጥ ውክልና መሠረት የጡረታ መዋጮ በመሰብሰብ ረገድ ከኤጀንሲው ጋር የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

$3. የኤጀንሲው ውሣኔዎች

1/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚሰጥ ለማናቸ ውም ዓይነት አበል ብቁ የሚያደርጉ ሁኔ ታዎች መሟላታቸው የሚረጋገጠውና የአ በሉ ዓይነትና መጠን የሚወሰነው በኤጀ ንሲው ይሆናል፡፡

2/ ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ውሣኔ የሚሰጠው የራሱን የመ ረጃ ማህደር፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ $2 መሠረት የሚተላለፉትን መረጃዎችና እንደ አግባቡ ባለመብቱ የሚያቀርባቸውን ተጨ ማሪ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ይሆናል፡፡

3/ በኤጀንሲው የመረጃ ማህደርና በሌላ አካል በቀረበለት ማስረጃ መካከል ልዩነት ቢፈጠር ተቀባይነት የሚኖረው ማስረጃ በኤጀንሲው ይወሰናል፡፡

3/ Where up on the date of the coming in to force of this Proclamation an employee separated from service and being receiving retirement pension benefit for life from pension fund transferred to the Private Organizations Employees Pension Scheme in accordance with sub-article (2) of Article 9 of this Proclamation, he shall continue to receive the same amount he has been receiving before the coming in to force of this Proclamation.

52. Obligation to Provide Evidentiary Data and Duty to Cooperate

1/ In accordance with the direction of the Agency any private organization shall collect, compile and submit to the Agency, in accordance with the form and within the time limit specified by the Agency, particulars and evidences relating to each of its employees which are necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ Any person shall furnish written evidence or appear and testify or give his opinion when so requested by the Agency for the purpose of implementing this Proclamation.

3/ Appropriate bodies shall have the duty to cooperate with the Agency in collecting pension contributions pursuant to delegations of powers under sub-article (4) of Article 11 of this Proclamation.

53. Decision of the Agency

1/ The fulfillment of conditions for entitlement to any kind of benefit payable in accordance with this Proclamation and the amount of the benefit shall be decided by the Agency.

2/ The decision of the Agency to be rendered in accordance with sub-article (1) of this Article shall be based on its own record, evidentiary data submitted to it in accordance with Article 52 of this Proclamation, and as may be appropriate, on additional evidences produced by the beneficiary.

3/ In the case of a difference between the records of the Agency and evidentiary data submitted to it, the prevailing evidence shall be decided by the Agency.

$4. ውሣኔን እንደገና ስለመመርመር

1/ ቅሬታ ያለው ባለመብት በሚያቀርበው ጥያቄ ወይም በራሱ አነሳሽነት ኤጀንሲው ቀደም ብሎ የሰጠውን ውሳኔ እንደገና ለመመርመር ይችላል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ $ የተደነገገው ቢኖርም ኤጀንሲው ውሣኔውን እንደገና ሲመረምር የአበል መሠረዝ፣ መቀነስ ወይም መቋረጥ ሊያስከትል የሚችል በቂ ምክንያት ያገኘ እንደሆነ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ሊሰረዝ፣ ሊቀነስ ወይም ሊቋረጥ በሚገባው አበል መጠን ክፍያው ታግዶ እንዲቆይ ማድረግ ይችላል፡፡

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ $ የተደነገገው ቢኖ ርም እንደገና በተደረገው ምርመራ የጡ ረታ አበል እንዲቀነስ ኤጀንሲው ከወሰነ ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌ ውጪ ያለአ ግባብ የጡረታ አበል ከተከፈለ ኤጀንሲው ከባለመብቱ አበል ላይ እየቀነሰ ለጡረታ ፈንዱ ገቢ የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

$5. ስለይግባኝ

1/ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ $3 ወይም አንቀፅ $4 መሠረት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ባለመብት በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 7)04/2ሺ3 አንቀጽ $7 ለተቋቋመው የማህበራዊ ዋስ ትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኝ የማቅረብ መብት ይኖረዋል፡፡

2/ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 7)04/2ሺ3 አንቀጽ $6 ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በግል ድርጅት ሠራተኞች የሚቀርቡ ይግባ ኞችን በሚመለከትም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

$6. ከግብር ነፃ ስለመሆን

በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚከፈል የጡረታ አበል፣ ከሚሰበሰብ የጡረታ መዋጮ እና ከጡረታ ፈንድ ኢንቨስትመንት ከሚገኝ ትርፍ ላይ ግብር አይከፈልም፡፡

$7. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1/ ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ለተፈጠሩ ህጋዊ ሁኔታዎች ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ ሕጎችና መመሪያዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

54. Review of Decisions

1/ The Agency may review its previous decision upon request by an aggrieved beneficiary or on its own initiative.

2/ Without prejudice to the provision of Article 50 of this Proclamation, where upon review, the Agency finds that there is reasonable ground for cancellation, deduction or termination of benefits, it may suspend payment to the extent the benefit is to be cancelled, deducted or terminated.

3/ Notwithstanding the provisions of Article 50 of this Proclamation, if the Agency, upon review, has decided to deduct the benefit or the benefit paid is contrary to this Proclamation, it shall have the power to deduct the amount paid thereof from the benefit of the beneficiary and transfer same to the Pension Fund.

55. Appeal

1/ A beneficiary who is aggrieved by the decision of the Agency made pursuant to Article 53 or Article 54 of this Proclamation shall have the right to lodge an appeal to the Social Security Appeal Tribunal established pursuant to Article 57 of Public Servants Pension Proclamation No. 714/2011.

2/ Article 56 of the Public Servants Pension Proclamation No. 714/2011 shall be applicable to employees of private organizations lodging appeals pursuant to sub-article (1) of this Article.

56. Tax Exemption

No tax shall be payable on benefits received, pension contribution collected and profits earned from investment of the Pension Fund, in accordance with this Proclamation.

57. Transitory Provisions

1/ Previous laws and directives shall remain applicable to legal situations created before the coming into force of this Proclamation.

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 0 መሠረት በወር ደመወዝ ላይ ተመሥርቶ የሚሰበሰበው የጡረታ ፈንድ መዋጮ፡-

ሀ) ከግል ድርጅት ሠራተኞች ይህ አዋጅ ከሚፀናበት ቀን አንስቶ ለመጀመሪያው ዓመት አምስት በመቶ /5በመቶ/፣ ለሁለተኛው ዓመት ስድስት በመቶ /6በመቶ/ እና ከሦስተኛው ዓመት ጀምሮ ሰባት በመቶ /7በመቶ/ ይሆናል፤

ለ) ከግል ድርጅቶች ይህ አዋጅ ከሚፀናበት ቀን አንስቶ ለመጀመሪያዉ ዓመት ሰባት በመቶ /7በመቶ/፣ ለሁለተኛው ዓመት ስምንት በመቶ /8በመቶ/፣ ለሦስተኛው ዓመት ዘጠኝ በመቶ /9በመቶ/ እና ከአራተኛው ዓመት ጀምሮ አሥራ አንድ በመቶ /01በመቶ/ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 09 እና አንቀፅ !3 መሠረት ለሚደ ረገው የአገልግሎት ጡረታ አበልና የጤና ጉድለት ጡረታ አበል ስሌት የሚያገለግለው መቶኛ ይህ አዋጅ ከሚፀናበት ቀን አንስቶ ለአንድ ዓመት 1.15በመቶ፣ ለሁለተኛው ዓመት 1.19በመቶ፣ ለሦስተኛው ዓመት 1.22በመቶ እና ከአራተኛው ዓመት ጀምሮ 1.25በመቶ ይሆናል፡፡

4/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ !1 እና አንቀፅ !5 መሠረት ለሚደረገው የአገልግሎት ዳረጎትና የጤና ጉድለት ዳረጎት ስሌት የሚያገለግለው የደመወዝ መጠን ይህ አዋጅ ከሚፀናበት ቀን አንስቶ ለአንድ ዓመት የ1.15 ወር ደመወዝ፣ ለሁለተኛው ዓመት የ1.19 ወር ደመወዝ፣ ለሦስተኛው ዓመት የ1.22 ወር ደመወዝ እና ከአራተኛው ዓመት ጀምሮ የ1.25 ወር ደመወዝ ይሆናል፡፡

5/ ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ አንቀጽ !9 የተጠቀሰውን የአካል ጉዳት መወሰኛ ሠንጠረዥ እስከሚያወጣ ድረስ የህክምና ቦርዶች የሚከተሉት አሠራር ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

6/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ %1 ድንጋጌ ቢኖርም የግል ድርጅት ሠራተኞችን በሚመለከት፡-

ሀ) የጡረታ መዋጮ መከፈል የሚጀምረው ከሐምሌ 1 ቀን 2ሺ3 ዓ.ም ጀምሮ ይሆናል፤

ለ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ $1/3/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጡረታ አበል መታሰብ የሚጀ ምረው ይህ አዋጅ ከሚፀናበት ቀን አንስቶ አንድ ዓመት ከሚሞላበት ቀጥሎ ካለው ወር ጀምሮ ይሆናል፡፡

2/ The pension contributions to be collected in accordance with Article 10 of this Proclamation shall, based on monthly salary, be:

a) from employees of private organization, five percent (5%) for the first year, six percent (6%) for the second year and seven percent (7%) as of the beginning of the third year from the effective date of this Proclamation;

b) from private organizations, seven percent (7%) for the first year, eight percent (8%) for the second year, nine percent (9%) for the third year and eleven percent (11%) as of the beginning of the fourth year from the coming into force of this Proclamation.

3/ The percentages to be used for the calculation of retirement pension and invalidity pension pursuant to Article 19 and Article 23 of this Proclamation shall be, 1.15% for the first year, 1.19% for the second year, 1.22% for the third year and 1.25% as of the beginning the fourth year after the coming into force of this Proclamation.

4/ The salary ratios to be used for the calculation of the retirement gratuity and invalidity gratuity in accordance to Article 21 and Article 25 of this Proclamation shall be, 1.15 month's salary for the first year, 1.19 month's salary for the second year, 1.22 month's salary for the third year and 1.25 month's salary as of the beginning of the fourth year from the effective date of this Proclamation.

5/ Until the Agency issues the schedule referred to in Article 29 of this Proclamation to determine the degrees of incapacity, the practices followed by medical boards shall remain applicable.

6/ Notwithstanding the provision of Article 61 of this Proclamation, with respect to employees of private organization:

a) payment of pension contributions shall start as of the 8th day of July, 2011;

b) without prejudice to the provision of Article 51(3) of this Proclamation, benefits shall commence to accrue as of the next month of one year after the effective date of this Proclamation.

$8. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ ኤጀንሲው ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

$9. ቅ ጣ ት

የያዘውን ማስረጃ በዚህ አዋጅ መሠረት ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም የዚህን አዋጅ ድንጋጌ አፈጻጸም የሚያሰናክል ተግባር የፈጸመ ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር እስከ 5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራትና እስከ ብር 0ሺ (አሥር ሺ ብር) በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

%. ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች

ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች ወይም ልማዳዊ አሰራሮች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆኑም፡፡

%1. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ 07 ቀን 2ሺ3 ዓ.ም

GR¥ wLdg×Rg S

yxT×eÃ ØÁ‰§ê ÄäK‰sÃê ¶pBIK PÊzÄNT

58. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Agency may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued pursuant to sub-article (1) of this Article.

59. Penalty

Whosoever is unwilling to submit evidentiary document under his possession or obstructs the implementation of this Proclamation is punishable, unless a higher penalty is prescribed in the Criminal Code, with rigorous imprisonment not exceeding 5 years and a fine not exceeding Birr 10,000 (ten thousand Birr).

60. Inapplicable Laws

No laws, or customary practices shall, in so far as they are inconsistent with this Proclamation, have force and effect in respect of matters provided for in this Proclamation.

61. Effective Date.

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 24th day of June, 2011

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA